በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ሐሰተኛ ተአምራት - 4


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ሰኔ ፲፰ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.**

# የመጨረሻው ዘመንና ሐሰተኛ ተአምራት

- ***2 ተሰ 2፡8-11፡፡*** ‹‹በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው፥ ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል፤ ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።››
- ሰይጣን ዋና ተቃዋሚያችን ሲሆን ሐሰተኛ መምህራንና ነቢያት አሉት፡፡ ***2 ጴጥ 2፡1*** ‹‹ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሾልከው ያገባሉ፤››፣ ሐሰተኛ ሐዋርያትና ወንጌላት አሉት፡፡ ***2 ቆሮ 11፡1-15***፣ ሐሰተኛ ተአምራት ያደርጋሉ፡፡ ***2 ተሰ 2፡9፡፡*** ‹‹በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው።››
- በመጨረሻውም ዘመን እነዚህ ሁሉ ተቀላቅለው የቤተ ክርስቲያንን ጎልውና የሚፈታተን ታላቅ የማሳሳት ሥራ ይሠራሉ፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ ሐሰተኛ ተአምራት በመጨረሻው ዘመን ሰዎችን ወደ ተሳሳተ ጎዳና እንደሚመሩ ሰባት ጊዜ ገልጾልናል፡፡ ***ማቴ 7፡21-23፣ ማቴ 24፡24፣ ማር 13፡22፣ 2 ተሰ 2፡8-12፣ ራዕ 13፡13-14፣ ራዕ 16፡14፣ ራዕ 19፡20፡፡***
- ይህም አሠራር በመጨረሻው ዘመን ከዓለም ውስጥ የሚበዙትን ሰዎች የሚያሳትፍ ይሆናል፤ ሰዎቹም የጠላት አገልጋዮች ሆነው ሳሉ በእግዚአብሔር ስም የክርስቶስ አገልጋዮች ነን ይላሉ፡፡
- እግዚአብሔር ከዲያቢሎስ ይልቅ የሚሠራ በርካታ እውነተኛ ተአምራትን የሚያደርግ አምላክ ቢሆንም ከሐሰተኛ ተአምራት ግን መጠንቀቅና መራቅ ይጠበቅብናል፡፡

# የመጨረሻው ዘመንና ሐሰተኛ ተአምራት

***አርቲስታዊ ገጽታ ያሳያሉ፡፡***

- ሰይጣን በሚሠራቸው ተአምራት እሳት ከሰማይ በትዕዛዝ ይወርዳል፣ ሰዎች ከሥጋቸው ደዌ ይፈወሳሉ፣ አውሬው ይገለጣል፣ ሰዎችም ለአውሬው ይገዙለታል፤ አውሬውም ማዕከላዊ አገዛዙን በዓለም ውስጥ ይዘረጋል - ‹‹ ለአውሬውም። አውሬውን ማን ይመስለዋል፥ እርሱንስ ሊዋጋ ማን ይችላል? እያሉ ሰገዱለት።›› ***ራዕ 13:4*** እንደተባለው ተከታዮቹ እንደርሱ ሰላምን በኃይሉ ያመጣ ማን ነው እያሉ ይሰግዱለታል፡፡
- ዓለምም ሁሉ በምትሐት ይታወካል፤ እግዚአብሔርና ክርስትና የማያስፈልጉ፣ ሥነ ምግባርም ጊዜ ያለፈበት ሆነው ይቆጠራሉ፡፡
- ሰዎችም በቅጽበት በሚያዩት ነገር ተማርከው ለራስ ወዳድነት፣ ለምትሐትና ለጥንቆላ አሠራር ተገዥ ይሆናሉ፡፡ ***ራዕ 13:11፡፡***
- ይህ ራሱን የሚያጸድቀው አውሬ ስለሚገባው ቃል፣ ስለ ታላላቅ ምልክቶቹ፣ በዓለም ላይም ከሚፈጥረው ኢኮኖሚያዊ ጫና የተነሣ የብዙዎችን ልብ በመማረክ ይገዛለታል፡፡
- ክርስቲያኖችም መከራ ይቀበላሉ፡፡ ጥቂቶችም ንስሐ ይገባሉ፡፡ የሚበዙት ግን በመተት/ጥንቆላ እንዲሁም በአመጻ ሥራቸው ጨክነው አርማጌዶን በተባለው ቦታ እስኪሰባሰቡና ከእግዚአብሔር ጋር ተዋግተው ድል እስኪደረጉ ድረስ ይዘልቃሉ፡፡

***በፍርድ ቀን ስለ ሐሰተኛ ተአምራት የሚፈረደው ፍርድ***

- ቅዱስ ጳውሎስ፣ ጴጥሮስ፣... ድንቅ ተአምራትን በእግዚአብሔር ስም በማድረግ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አቅርበዋል፡፡
- ***ማቴ 7:21-23*** ‹‹ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። በዚያ ቀን ብዙዎች። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም። ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።››

# የመጨረሻው ዘመንና ሐሰተኛ ተአምራት

***በፍርድ ቀን ስለ ሐሰተኛ ተአምራት የሚፈረደው ፍርድ***

- ለዚህ ያበቃቸውም ተአምሩ ሳይሆን ይህን ተአምር እንዲያደርጉ ከልባቸው የመነጨው ጥፋት ነው፡፡ እነዚህም የሚያስፈርድባቸውን ተአምራት የሚያደርጉ ክፋትን የተሞላ ትምክህተኛና ኩሩ ልብ፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚመራ ሕይወትና ለቅድስናም ንቀት ያላቸው የእግዚአብሔርን ስምና ኃይል ከባሕርዩ፣ ክርስቲያናዊ ሥራንም ከዓላማው ለይተው የሚጠቀሙ ‹‹የክርስቲያን ጠንቋዮች›› ናቸው፡፡
- ሐሰተኛ ተአምራት በቤተ ክርስቲያን ያሉትን ሳይቀር ያስታሉ
- ‹‹ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ።›› ***ማቴ 24፡24፣ ማር 13፡22*** እንደተባለው እግዚአብሔር የራሱን ምርጦች ይጠብቃቸዋል እንጂ እነዚህ ተለይተው በራሳቸው የሚንቀሳቀሱ ራሳቸውን ‹‹መሲሕና›› ‹‹ነቢይ›› ያደረጉ የእግዚአብሔርን አገልጋዮችና አማንያን ሳይቀር ያስታሉ፡፡
- ከፊሊሞና በቀር የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔርን ሰዎች ስለሚያስቱት ስለነዚህ ሐሰተኞች በስፋት ጽፈውልናል፡፡ ***ፊል 1፡9-11፣ ቆላ 1፡9-10፣ ቀዳ ዮሐ 4፡13፡፡***
- ታዲያ እነዚህን ስተው የሚየስቱትን እንዴት ለይተን እናውቃቸዋለን? ከሁሉ አስቀድሞ ***በማቴ 22፡37-40*** እንደተጻፈልን እግዚአብሔርንና ባልንጀራችንን ከልብ መውደድ ክፉውን ከሐሰት የመለየት ጥበብን ያድለናል፡፡ ይህን ይዘን የሚከተሉት መለኪያዎቻችን ናቸው፡-
    1. በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ያምናሉ? ***ቀዳ ዮሐ 4፡15፡፡*** ‹‹ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በሚታመን ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራልና።››
    2. እግዚአብሔር በሥጋ እንደተገለጠ ያምናሉ? ***ቀዳ ዮሐ 4፡1-4፡፡*** ‹‹ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና። የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፥ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል፥ አሁንም እንኳ በዓለም አለ። ልጆች ሆይ፥ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋቸውማል፥ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና።››
-

# የመጨረሻው ዘመንና ሐሰተኛ ተአምራት

## *በፍርድ ቀን ስለ ሐሰተኛ ተአምራት የሚፈረደው ፍርድ*

- ይህን ይዘን የሚከተሉት መለኪያዎቻችን ናቸው፡-

3. ራሱን እንደ ክርስቶስ ይቆጥራል? ***ማቴ 24፡23-24፡፣ ማር 13፡21-22፣ ካል ቆሮ 11፡13-15፡*** ‹‹በዚያን ጊዜ ማንም፡፡ እነሆ፥ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም፡፡ ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ፡፡››
4. የመንፈስ ፍሬዎች የሆኑት ፍቅር ፣ ቸርነት፣ እምነት … አሉት? ወይስ ራሱን ብቻ ሕግን በማፍረስ ራሱን ብቻ ደስ የሚያሰኝ ነው? ***ማቴ 7፡15-20፡፡*** ‹‹የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ፡፡ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፡፡ ከእሾህ ወይን ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል፡፡ መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት፥ ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም፡፡ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል፡፡ ስለዚህም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፡፡›
5. ሐሰተኛ ተአምርን የሚያደርግ በሌሎች ክርስቲያኖች ሕይወት ወይም በአገልግሎታቸውም ላይ ፍጹም ጥላቻ ያለውና ፍርድም የሚፈርድ ነው? ከሆነ ይህ ከጨለማ ለመሆኑ ፍጹም ምስክር ነው፡፡ ***ቀዳ ዮሐ 2፡8-11፣ 3፡15-18፣ 4፡20-21፡፡***
6. ሰዎችን ስለ ምግብ፣ ጋብቻ፣ በዓላት፣ ሰንበት … እንግዳ ትምህርትና ሥርዓት በማስተማር ባሪያ የሚያደርጉ ይሆናሉ፡፡ ***ቆላ 2፡16-23፣ ቀዳ ጢሞ 4፡1-7፡፡*** እውነተኛውን ተአምራት የሚያደርጉት እውነተኞች ግን ሕዝብን ነጻ የሚያወጡ ይሆናሉ፡፡ ***ዮሐ 8፡32-36፣ ገላ 5፡1፡፡***
7. ተከታዮቹን ራሱን ወይስ ክርስቶስን እንዲከተሉ ያደርጋቸዋል? ***የሐዋ 20፡20፡፡*** ‹‹ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኵላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ።››
8. ለገንዘብ ስግብግብና ዓለምንም የሚወድ ነው፡፡ ‹‹ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኵላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ።›› ***ቲቶ 1፡11፣ 2፡12፣ ይሁዳ 11፣ ያዕ 4፡4፣ ቀዳ ዮሐ 4፡1-6፡፡***
9. ትምህርተ ሃይማኖትን ትቶ ፍልስፍናንና የአሮጊቶችን ሴቶች ጨዋታ የሚያስተምር ነው፡፡ ***ቀዳ ጢሞ 4፡1-7፣ ቆላ 2፡8-10፡፡***

-

# የመጨረሻው ዘመንና ሐሰተኛ ተአምራት

## ***በፍርድ ቀን ስለ ሐሰተኛ ተአምራት የሚፈረደው ፍርድ***

- ይህን ይዘን የሚከተሉት መለኪያዎቻችን ናቸው፡-
  10. ሌሎችን አይወድም፣ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አይሳተፍም (ቅዳሴ፣ ሰዓታት፣ ማኅሌት፣ ኪዳን…)፣ የክርስቶስ አካል ከሆነች ቤተ ክርስቲያንም ተለይቶ ለተአምር ሥራው ብቻ የሚመጣ ነው፡፡ ‹‹ልጆች ሆይ፥ መጨረሻው ሰዓት ነው፥ የክርስቶስም ተቃዋሚ ይመጣ ዘንድ እንደ ሰማችሁ አሁን እንኳ ብዙዎች የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ተነሥተዋል፤ ስለዚህም መጨረሻው ሰዓት እንደ ሆነ እናውቃለን። ከእኛ ዘንድ ወጡ፥ ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉ ከእኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገለጡ ዘንድ ወጡ፡፡›› ***ቀዳ ዮሐ 2፡18-19፣*** ‹‹እኛ ከእግዚአብሔር ነን፤ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል፤ ከእግዚአብሔር ያልሆነ አይሰማንም። የእውነትን መንፈስና የስሕተትን መንፈስ በዚህ እናውቃለን።›› ***ቀዳ ዮሐ 4፡6፡፡***
- ‹‹የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን?›› ***ማቴ 7፡15-16፣ ይሁ 4-19፡፡***
- እነዚህ ንግግር የሚያምርላቸው፣ ስለ ራሳቸው የሚጨነቁ፣ ዓለማውያን፣ የእግዚአብሔርን ነገር ቸል የሚሉ፣ የራሳችን አገልግሎት ከሚሉት በላይ ያለውን ማንኛውንም ባለሥልጣን - ሥልጣንና - ትእዛዝ የማይቀበሉ ናቸው፡፡
- እንግዲህ ሐሰተኞች እንደዚህ ከሆኑ እውነተኛነታቸውን የመጠራጠር ሙሉ መብት አለን፡፡
- እውነተኞቹ የታማኝነት፣ የፍቅርና፣ የአንድነት ሕይወት አላቸው፤ ክርስቶስን የሚመስሉ ትሑታን ናቸውና ከነዚህ የሚለይ ግብር ያላቸውን ሁሉ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ***ቀዳ ዮሐ 4፡1-4፡፡*** ምርመራችንም እውነተኛ፣ ቀናና ታማኝ መሆናቸውን ከመመርመር ያለፈ መሆን የለበትም፡፡

## ***በመጨረሻው ዘመን የዓለም ሁሉ መሳሳት***

- ***ካል ተሰ 2፡8-11፡፡*** እንደተጠቀሰው ከሐሰተኛ ተአምራት ጀርባ ያለው በርግጥም ዲደደቢሎስ ነው፡፡ ከተአምራቱም ጀርባ ሕግን ወደ መጣስ የሚያደርስ ስህተት አለ፤ የስህተቱም ተጠቂዎች ‹‹ዘወትር ተምረው እውነት ወደ ማወቅ የማይደርሱ እምቢተኞች›› ናቸው፡፡
- እግዚአብሔር ስንፍናንና ምግባረ ብልሹነትን የሚጠላ አምላክ ነው፡፡

# የመጨረሻው ዘመንና ሐሰተኛ ተአምራት

***በመጨረሻው ዘመን የዓለም ሁሉ መሳሳት***

- ***በራዕ 13፡11-18፣ ራዕ 16፡12-14፣ ራዕ 19፡20*** እንደተጻፈው የሐሰተኛ ተአምራት ዋና ዓላማቸው/ግባቸው አንድ ሲሆን እርሱም ዓለምን በጣዖት አምልኮ ሥር ማሰባሰብ ነው፡፡ ***ራዕ 13፡14፣ ማቴ 24፡24፣ ማቴ 7፡22፣ ራዕ 16፡13-14***
- የዚህ ስህተት ዒላማዎች የዓለም መሪዎች ናቸው - ከእነዚህም የሚያስተው መንፈስ ለጦርነት ይሰበስባል፡፡ የመሰብሰቢያው መረብም ሰፊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ለማግኘት ሀብትን ለማከማቸት ስግብግብ የሆኑትን ሁሉ የሚስብና የሚያጠምድ ነው፡፡ ‹‹ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፥ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር። በፊተኛውም አውሬ ሥልጣን በእርሱ ፊት ሁሉን ያደርጋል። ለሞቱ የሆነውም ቍስል ተፈወሰለት ለፊተኛው አውሬ ምድርና በእርሱ የሚኖሩት እንዲሰግዱለት ያደርጋል። እሳትንም እንኳ ከሰማይ ወደ ምድር በሰው ፊት እስኪያወርድ ድረስ ታላላቆችን ምልክቶች ያደርጋል። በአውሬውም ፊት ያደርግ ዘንድ ከተሰጡት ምልክቶች የተነሣ በምድር የሚኖሩትን ያስታል፤ የሰይፍም ቍስል ለነበረውና በሕይወት ለኖረው ለአውሬው ምስልን እንዲያደርጉ በምድር የሚኖሩትን ይናገራል። የአውሬው ምስል ሊናገር እንኳ ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ ሊያስገድላቸው፥ ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው። ታናናሾችና ታላላቆችም ባለ ጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ፥ የአውሬውም ስም ወይም የስሙ ቍጥር ያለው ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደርጋል። ጥበብ በዚህ አለ። አእምሮ ያለው የአውሬውን ቍጥር ይቍጠረው፤ ቍጥሩ የሰው ቍጥር ነውና፥ ቍጥሩም ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ነው።›› ***ራዕ 13፡11-18፡፡***
- በእርግጥ እግዚአብሔር ስማችንን በሕይወት መጽሐፍ ካልጻፈ በዚህ ስህተትና የስህተት አሠራር ሥር እንወድቃለን፡፡ ‹‹ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ።›› ***ራዕ 13፡8፣ ካል ተሰ 2፡10፣ ካል ተሰ 2፡9፡፡***

# የመጨረሻው ዘመንና ሐሰተኛ ተአምራት

***ማጠቃለያ***

- በመጨረሻው ዘመን በሚያስፈራው ሐሰተኛ አሰራር ብንፈተንም እንዳንፈራ ወይም ተስፋ እንዳንቆርጥ በእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ስጦታዎች፣ ተአምራቷ፣ … መጠበቅ ይኖርብናል፡፡ ይህን ካደረግን ሐሰት አቅም/ጉልበት ያጣልና ወደ ተወደደችውና እግዚአብሔር ምስክር ወደ ሆነላት ቤተ ክርስቲያን እንቅረብ፡፡
- የቤተ ክርስቲያን የሆን ሁሉ አሁን ኃይልንና፣ ጽድቅን መጎናጸፍ፣ ተአምራቱንና ምልክቶቹን፣ ቃሉንና ምስጢሩን፣ ዶግማውንና ሥርዓቱን፣ ፍቅሩንና ጣዕሙን ገንዘብ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡
- እንክርዳድ የሚዘራው በጠላት ሲሆን በመልካም የአትክልት ሥፍራ የሚኖረው አበባ ሁሉ ቀንሞስ ብቻ እንዳልሆነ አስተውለን ተአምራትን በተመለከተ በመጨረሻው ዘመን በጥበብ፣ መነዋወጽ በሌለባት ጽኑ አቋም መጓዝ ይጠበቅብናል፡፡
- በመጨረሻም ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ተአምራት የጻፈልንን መልእክት በመጥቀስ በዚህ ርዕስ የጀመርነውን ትምህርት እናጠቃልላን፡፡ ‹‹አሕዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በሥራ፥ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል፥ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእኔ አድርጎ ከሠራው በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም፤ ስለዚህ ከኢየሩሳሌም ጀምሬ እስከ እልዋሪቆን ድረስ እየዞርሁ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ፤ ሰብኬአለሁ። እንዲሁም በሌላው ሰው መሠረት ላይ እንዳልሠራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ስፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ፤ ነገር ግን። ስለ እርሱ ያልተወራላቸው ያያሉ፥ ያልሰሙም ያስተውላሉ ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።›› ***ሮሜ 15፡18-21፡፡***
- ተአምራት የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥባቸው ፍቅሩን ያሳየባቸው ወደ እምነት የሚስቡን ናቸው፡፡
- ተአምራትንም በስሜታችን ብቻ ከመመርመር በእምነት መመርመር የክርስትናችን ምልክት እንደሆነ ያረጋግጥልናል፡፡ ***ኤር 17፡9፡፡***

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org